# እንኳን ከነመራራ ጉዲና ጋር ተጎዳኝተው በራስዎም ቢወዳደሩ የመቀሌ ህዝብ አይመርጥዎትም

ለ አቶ ገብሩ አስራት

ከመርስኤ ኪዳን

እንዳሁኑ ሳይሆን ቀድሞ "ገብረማሪያም" ምርጥ ከሚባሉ ስሞቸ አንዱ ነበር። እናም አንዳንድ አይነደረቅ ሰዎችን ለመግለፅ በትግርኛ "ዘይሓፍር ድሙ ገብረማሪያም ሽሙ" የሚል አባባል አለ። ትርጉሙም "የማያፍር ድመት ስሙ ገብረማሪያም ነው" ማለት ነው። ይህን አባባል ለመጠቀም ያስገደደኝ በምርጫ ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ባለፈው ሳምንት በተደረገው ክርክር መድረክን ወክለው የተገኙት ሰው አቶ ገብሩ አስራት መሆናቸውን ሳይ የተፈጠረብኝ ግርምት ነው። የክርክሩ አጀንዳ ሰብአዊ መብት፣ የህግ የበላይነትና መልካም አስተዳደር ስለነበር ነው ግራ መጋባቴ። ምክኒያቱም አቶ ገብሩ የትግራይ ፕሬዝዳንት እያሉ ትግራይ ውስጥ የዩንቨርስቲ ተማሪ ስለነበርኩ የሳቸው አስተዳደር ምን ይመስል እነደነበር ጠንቅቄ ስለማውቅ ነው።

አቶ ገብሩ በክርክሩ የተሰጣቸውን 8 ደቂቃ በሙሉ የተጠቀሙት ኢህአዴግን በመውቀስ ነው። በርግጥ በሰብአዊ መብት አያያዝ ጉዳይ ችግር ያለበት መንግስት በመሆኑ ብዙም የሚያስገርም አይሆንም። እኔን ያስገረመኝ የወቃሹ ማንነት ነው። አቶ ገብሩ አስራት በስልጣን ዘመናቸው ባገሪቱ የከፋ የሚባለውን አፋኝ አስተዳደር ያቋቋሙና (የትግራይ ክልል በሳቸው ጊዜ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል የከፋ የሙብት ጥሰት የሚፈፀምበት ነበረ። ያለምንም ጥርጥር ከሳቸው በሁዋላ ይሻላል።) በ ኢህአዴግ ክፍፍልም ወቅት በዴሞክራሲያዊነት ጉዳይ ችግር የለብንም ችግራችን የሉአላዊነት ጉዳይ ብቻ ነው ብለው የተከራከሩ ናቸው። ከዚያም በሁዋላ ብዙ ትግሬዎችን ባሳዘነና ባሳፈረ ሁኔታ አቶ በድሩ አደም "ወደመጡብት እንመልሳቸዋለን" የሚለውን ንግግራቸውን ባሰሙበትና "ንበረት ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደመቀሌ" ተብሎ መፈክር በተሰማበት ስብሰባ ተገኝተው ቡራኬ የሰጡ ሰው ናቸው።

አቶ ገብሩ የ ኢህአዴግ መሰረታዊ ችግር ሌሎችን በጠላትነት መፈረጁ ነው። በማለት ነው ክርክራቸውን የጀመሩት። ይህን ስሰማ ጆሮዬን ማመን ነው ያቃተኝ። ምክኒያቱም በኢህአዴግ ውስጥ ሌሎችን በጠላትነት በመፈረጅ የተሰጣቸውን የህዝብ አደራ ጭምር በመጠቀም ከሕወሓት በስተቀር አንድም ፓርቲ በትግራይ ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ አፍነው ይዘው የነበሩት አቶ ገብሩ ዛሬ እንዲህ ማለታቸው ወቸጉድ የሚያሰኝ ነው። በሳቸው ፕሬዝዳንትነት ጊዜ እንኩዋን ሌላ ፓርቲ በትግራይ ውስጥ ብዙ ደጋፊዎች እንዳሉት የሚታወቀው ኢዲዩ ቢሮ እንኩዋን ለመክፈት ሳይፈቀድለት አባላቱም ወደትግራይ መግባት እንዳይችሉ ታግደው ከፍተኛ አፈና ይፈፀምባቸው እንደነበር አለም ያወቀው ሓቅ ነው። በዚህ አጋጣሚ ከተሃድሶው በሁዋላ ኢህአዴግ ከፍተኛ ለውጥ እንዳመጣ መመስከር እፈልጋለሁ። በትግራይ ውስጥ ባሁኑ ጊዜ ብዙ ፓርቲዎች ቢሮ ከፍተው በተሻለ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል።

እንዲህ ጠንቅቀን ለምናውቃቸው ሰዎች ያቶ ገብሩ አስራት ደርሰው የዴሞክራሲ ጠበቃ መሆን "አያ ጅቦ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ" እንዳለው መሆኑ ነው። አቶ ገብሩ አስራት ወቀሳቸውን ሲያቀርቡ "ለምንድነው መምህራን የ ኢህአዴግ አባል እንዲሆኑ የሚገደዱት?" "ለምንድነው የትምህርት እድል ለማግኘት የፓርቲ አባልነት ግዴታ የሆነው?" ሲሉ በጥያቄ መልክ አቅርበዋል። ማንን ቅንደሚጠየቁ ግራ ገባኝ። በክርክሩ ኢህአዴግን ወክለው የተገኙት የትምህርት ሚኒስትሩ አቶ ደመቀና አቶ ሬድዋን እንደሆነ እነሱም ተመልምለው

አባል የሆኑ እንጂ በዚህ መጠየቅ ያለባቸው አይመስለኝም። በክርክር ውስጥ ከነበሩት ሰዎች በዚህ ጉዳይ ሊጠየቅ የሚችለው ራሳቸው አቶ ገብሩ አስራት ብቻ ናቸው። እስኪ ራሳቸው ይመልሱ። እሳቸው ፕሬዝዳንት በነበሩበት ጊዜ ከ ኢህአዴግ አባል በስተቀር የመንግስት ስራ ማግኘት ይችል ነበር? እርስዎ በ ኢህአዴግ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልነትዎ ጊዜ በስትራቴጂ መልክ ያረቀቁትን መመሪያ አሁን ደርሰው "ለምንድነው?" ብለው ሲጠይቁ አለማፈርዎ ነው "ዘይሓፍር...." ያሰኘኝ።

አቶ ገብሩ ይባስ ብለው በ ኢህአዴግ አመራር ዘመን ብቃት ያለው ነፃ ፕሬስ አለመኖር የሰብአዊ መብት ጥሰትን አባብሷል ሲሉ አደመጥኩ። በርግጥ የፕሬስ ነፃነት አደጋ ውስጥ እንዳለ ሁላችንም የምናውቀው ሃቅ ስለሆነ ብዙም የሚገርም አይደለም። የሚገርመው በዚህ ጉዳይ ከሳሹ ዋነኛው የዚህ ሁኔታ ፈጣሪ አቶ ገብሩ መሆናቸው ነው። ትዝ ይለኛል አቶ ገብሩ የትግራይ ፕሬዝዳንት በነበሩበት ጊዜ ከወይን ጋዜጣና ከድምፅ ወያነ በስተቀር አንድም የፕሬስ ውጤት ወይም ሚዲያ እንዳልነበር። ሪፖርተር ጋዜጣ እንኳ ድንገት ካዲስአበባ ሰው ሲያመጣልን ተደብቀን ነበር የምናነበው። ታዲያ በስልጣን ዘመናቸው ሆን ብለው አንድም የግል ጋዜጣ በክልላቸው እንዳይታተምም ሆነ እንዳይሸጥ አግደው የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት አሁን የነፃ ፕሬስ እጦት የሰብአዊ መብት አያያዝን አባብሷል ሲሉ ማድመጥ በትግርኛው "ጩግራፍያ ባዕላ ሃሪማ ባዕላ ተእውይ" "ጅራፍ ራሷ ገርፋ ራሷ ትጮሃለች" እንደሚሉት ሆነብኝ። አቶ ገብሩ እወራረድዎታለሁ በትግራይ ውስጥ እርስዎ በስልጣን ላይ ከነበሩበት ጊዜ በተሻለ የፕሬስ ነፃነት አሁን አለ። አሁን ያለውን የፕሬስ ሁኔታ መተቸት የሚችለው የተሻለ አመለካከት ያለው ሰው እንጂ እርስዎማ.....

በዚህ እየተገረምኩ እያለሁ አቶ ገብሩ ይባስ ብለው ስለድርቅ አነሱ። 13 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ በድርቅ ተጠቅቶ እያለ ኢህአዴግ በኢኮኖሚ አገሪቷን አሳድጌአለሁ ይላል ሲሉ ተቹ። ገበሬዎች እዳ መክፈል አቅቷቸዋል በማለትም አማረሩ። አቶ ገብሩ አንድ ነገር ልንገርዎ፤ እኔ በትግሬነቴ በጣም ያፈርኩበትና ያዘንኩበት ጊዜ ቢኖር የዛሬ አስር አመት ገደማ እርስዎ የትግራይ ፕሬዝዳንት በነበሩ ጊዜ በትግራይ የደረሰው ድርቅ በተጎጂዎቹ ላይ ያደረሰውን መንፈሳዊና አካላዊ ውድቀት የተመለከትኩ ጊዜ ነው። በዚያን ጊዜ መቀሌ ፓሪስ ሆናለች እየተባለ በሚወራበት ወቅት ከመቀሌ ብዙም የማትርቀው ሳምረ የምትባል አካባቢ የነበሩ ህዝብ በድርቅ ተጠቅተው አምና የተበደሩትን አንድ በሬ መክፈል አቅቷቸው የተሰደዱበት፤ አዲስአበባም ባስርሺዎች በሚቆጠሩ ከትግራይ በመጡ የኔቢጤዎች የተሞላችበት ጊዜ ነበር። አንድ ቀን በታክሲ እየተጓዝኩ አንድ ፈርማታ ጋር አንድ ከትግራይ የመጣች የኔ ቢጤ ታክሲውን ጠጋ ብላ የተኮላተፈ አማርኛና ትግርኛ እየደባለቀች ስትለምን፣ አንዱ ተሳፋሪ "አንቺ ዞርበይ ካጠገቤ ዘመዶችሽ ከላይ እናንተ ከታች ሆናችሁ እኛ የት እንሂድላችሁ" ብሎ ሲያመናጭቃት ተመለከትኩ። በሂወቴ እንደዛን ቀን አዝኜ አላውቅም። አቶ ገብሩ ይህ ሁሉ ሲሆን እርስዎ የትግራይ ፕሬዝዳንት ነበሩ። ከ1977ቱ ድርቅ ወዲህ በትግራይ የከፋው ድርቅ የተከሰተው በርስዎ ፕሬዝዳንትነት ጊዜ ነው። ታዲያ አሁን ደርሰው የቀድሞ ጓዶችዎን በድርቅ ሲከሱ ለተመልካቹ ከማስገረም አልፎ "የምን አይነደረቅ ተመልሶ ልብ ያድርቅ" ከማለት ሌላ ምን ሊባል ይችላል። አንድ ነገር በርግጠኝነት ልንገርዎ፤ ትግራይ ከርስዎ ፕሬዝዳንትነት ከተገላገለች ወዲህ እጅግ በጣም በተሻለ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ይህን እርስዎም አይኔን ግንባር ያርገው ካላሉ ሊክዱት አይችሉም።

አቶ ገብሩ ለጥቀው የስልጣን ጥማት የለብኝም ጥማት ቢኖርብኝ ከኢህአዴግ ጋር ነበር የምለጠፈው ብለው ሊያሞኙንም ሞከሩ። በመጀመሪያ ደረጃ እርስዎ ሺህ ቢለምኑ ኢህአዴግ እንደማያስጠጋዎ እያወቅን ስልጣን ብፈልግ ከኢህአዴግ እጠጋ ነበር ማለት ተጨፈኑ ላሞኛችሁ እንደማለት ነው። ኢህአዴግ እንኳን እርስዎን ሊያስጠጋ የተሃድሶ ፈተናውን ያለፉትን የቀድሞ ጓዶችዎን ባዳዲስ አመራሮች እየተካ ነው። ጓደኛዎ እርስዎን ለማፅናናት ይሁን ለፕሮፓጋንዳ "ገብሩ በመቀሌ ተሸነፈ ማለት ዘበት ነው" ሲሉ ተደምጠዋል። እንግዲህ በመቀሌ ጎዳናዎች ተዘዋወሩና ጠይቁ እንኳን ከነመራራ ጉዲና ጋር ተጎዳኝተው በራስዎም ቢወዳደሩ የመቀሌ ህዝብ እንደማይመርጥዎ እወራረድዎታለሁ። አቶገብሩ በትጥቅ ትግሉ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ሁላችንም

እናከብርዎታለን የርስዎም ሆነ የጓዶችዎ ስራ ለዘላለም ሲዘከር ይኖራል። በዚያው መጠን አሁን በሚሰሩት ስራ እናፍርብዎታለን። ይህም ለዘላለም ሲዘከር ይኖራል።

በተረፈ የትግራይ ህዝብ እንደሌላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ ወደፊት እንጂ ወደ ሁዋላ የሚያይበት ሁኔታ ላይ ስላይደለ አዝንልዎታለሁ። ህዝቡ እንኳን ወደሁዋላ ሊመለስ አሁን ያለውም አልበቃ ብሎት የበለጠ ዴሞክራሲን የበለጠ ነፃነትን የበለጠ እድገትን በመጠየቅ ላይ ይገኛል። ለዚህም መልስ የሚሰጡት እንደርስዎ የቀድሞ ማርክሲስት ያሁን ስልጣኒስት ፖለቲከኞች ሳይሆን ባዲሱ ትውልድ የሚመሩ የወደፊት ፓርቲዎች ናቸው።

መርስኤ ኪዳን

መጋቢት 2002 ዓ.ም

Mersea@ethiopiandemocrats.com